# ሌባ ዘር የለውም

ሰብዓዊነት የለ ፣ ይሉኝታን አያውቁ
በደም የታጠቡ ፣ የተጨማለቁ
ቢሰርቁ ቢበሉ ፣ ሁሌ እማይጠረቁ
እነ ሁሉ አማረሽ ፣ እነ ሁሉ ብርቁ
ወደኋላ የለም ፣ ተባዮች ሳያልቁ ።

ህዝብ እየታገለ ፣ ከጨቋኝ ገዳዩ
ቁብ የማይሰጣቸው ፣ የሀበሻ ስቃዩ
27 ዓመት ፣ ሲዘፍኑ የቆዩ
ግፍና መከራን ፣ አንዱንም ያላዩ
የጡት አባታቸው ፣ መውደቁን ስላዩ
የሌባ ዘራፊ ፣ አጋር ሆነው ታዩ
ዛሬም እንደ ትላንት ፣ ለመጫን ከላዩ ።

አመልና ጭራ ፣ ሁሌም በስተኋላ
እርሟን ብታፈላ ፣ ጋን ሙሉ አተላ
አንገት እንዳትደፋ ፣ ሰርቆ ስላበላ
ሰልፍ ወጣች ተባለ ፣ ለሌቦ ከለላ
መች ህሊና አለና ፣ ከእግዜር ለተጣላ ።

በጅምላ የሚያስቡ ፣ የሆኑ ኅጠኞች
ሟችን የሚከሱ ፣ ፍርደ ገምድል ዳኞች
አዝለው እየኖሩ ፣ ሆዳም የቀን ጅቦች
አይናቸውን በጨው ፣ የታጠቡ ጉዶች
አሚና ለፍላፊ ፣ አስልቺ አደንቁሮች ።

ከደሃ የሚቀማ ፣ እያስለቀሰ እንባ
እንኳንስ ካዝና ፣ ከኪስ የሚገባ
ወራዳ ቅሌታም ፣ ቀላል ከገለባ
ተብለን ነበረ ፣ ዘር የለውም ሌባ
አለን ብለው መጡ ፣ ጆሮ ልበስ ዳባ
የሚተነፍሱ ፣ ያውም ባንድ ሳንባ ።

በኅጠኞች ተረት ፣ ተተብትቦ ታስሮ
ካሰበ እንደ እንሰሳ ፣ ከሌለው አይምሮ
ህዝብ እያለቀሰ ፣ የማይሰማ ጆሮ
የሌቦቹን መንጋ ፣ ሸሽጎ ከጓሮ
ዘራፊና ገዳይ ፣ ሲታሰር እሮሮ
የተገላቢጦሽ ፣ ጭራሽ ከተፈጥሮ
ሌባ ዘር የለውም ፣ አትበሉን ዘንድሮ
አይናችሁ እያየ ፣ ዘመን ተቀይሮ ።

ታዛቢው

November 26, 2018